# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል ሃያ-ሦስት (ከክፍል ሃያ-ሁለት የቀጠለ)፤-..</u>***

ሐ) ከፖሊስ፣ ከፀጥታና ከጦር ኃይል ክፍሎች ጋር የሚገናኝ አንድ የደኅንነትና የመረጋጋት ጉዳይ የጋራ አካል በማቋቋም፤
መ) የአገዛዙን ግትርነትና መሠሪያዊ ባኅሪ ባገናዘበ ሁኔታ በግልጥ መመሪያ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት እንዲሁም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደራደር አንድ ተደራዳሪ የጋራ አካል በማቋቋም፣ መርኅን ያልለቀቀና የሕዝቡን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ድርድር እንዲደረግና ይዘቱንም ሕዝብ እያወቀው እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በዚኽም ረገድ የተጠናከረ የጋራ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ጥረት አድርጓል።

እነዚኽን እንቅስቃሴዎች በጋራ በማድረግ በአንድ በኩል ተቃዋሚው ጠንካራ መርኅን የተመረኮዘ አንድነት እንዳለውና በሁለቱም በኩል የሕዝቡን ድምፅ ለማስከበር ተመሣሣይና የማይነጣጠል ፍላጎትም ቁርጠኝነትም እንዳላቸው በግልጥ በማሣየት ሕዝቡም፣ አገዛዙም ሆነ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡ በማያወላዳ ሁኔታ እንዲያውቁት ማድረግ፤ በሌላ በኩል ትግሉ ሕዝባዊ መሠረቱን እያሠፋ አገዛዙ ሕዝቡ በክቡር መስዋዕትነቱ ያስመዘገባቸውን ድሎች በቀላሉ እንዳይቀለብስ ውስጣዊ ድርጅታዊ ይዞታውን በየፈርጁ ማጠናከርና ሕዝባችንን ለቀጣዩ ምዕራፍ በማዘጋጀት ትግሉን መዘዙ ከበዛ ቅልበሣ ማዳን ይቻላል ከሚል እምነት እንደሆነ ግልጥ ነው። ሆኖም ግን ቀደም-ሲልም እንደተገለጠው ሁሉ እነኝኽ አሣቦች ከኅብረቱ መውጣታቸውን እንጂ በሙሉ፣ በቅጡና በጊዜው ወይም ምን ያኽሉ ለሁሉም የቅንጅት አመራር አባላት መድረሣቸውን ሙሉ-በሙሉ ማረጋገጥ የሚቻል አይመስለኝም።

ድኅረ-ምርጫ ሁለቱ ድርጅቶች (ቅንጅትና ኅብረት) ሰተት ብለው በኢሕአዴግ የተሰላ አሰናካይ ወጥመድ ውስጥ እራሣቸውን ያስገቡበትና ትግሉን ለቅልበሣ ያመቻቸ የመጀመሪያው ከፍተኛ ስህተት የተፈጸመው "የሦስትዮሽ ስምምነት" የተባለውን "ውል" ሰኔ ሦስት ቀን የሁለቱ ድርጅቶች "ተወካዮች" መፈረማቸው ነበር። ይኽ ሰኔ አንድ ቀን ዘጠና-ሰባት ዓ/ም 'የሕዝብ ድምፅ ይከበር' ብለው በጠየቁ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ በአቶ መለስ አገዛዝ የተወሰደውን አረመኔአዊ የጭፍጨፋ እርምጃ ምክንያት አድርጎ በ"ሰላም" ስም በቅንጅት፣ በኅብረትና በኢሕአዴግ መኻል የተፈጸመ "የሦስትዮሽ ውል" ኢሕአዴግ የሕዝቡን ድል እንዲቀለብስ በር የከፈተለትና "ሕጋዊ" ሽፋን የሰጠ ከፍተኛ ስህተት ነበር። በመሆኑም ነው ባድመን ሰበብ አድርጎ ሽዓብያ በተነኮሰውና የብዙ አሥርተ-ሽህዎችን ሕይዎት የቀጠፈው ጦርነት የወራሪው የኢሣኢያስ ጦር አይቀጡ ቅጣት ከተቀጣና አዋራጅ ሽንፈትን ከተከናነበ በኋላ ዕድሜ ለአቶ መለስ በመራር መስዋዕትነት የተገኘን ድል አሣልፎ እንደሰጠው "የአልጀርስ ስምምነት" ሁሉ በበኩሌ የሰኔን የሕዝብ ድሎች አሣልፎ የሰጠ ያን የሰኔ ሦስት "የሦስትዮሽ ውል" 'ዳግም የአልጀርስ ስምምነት' ልለው የደፈርኩት።

የሆነ-ሆኖ የኅብረቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ በአንድ ተወካዩ ተፈረመ የተባለውን ያ "ውል" ባይቀበለውም አገዛዙ እንዳሰላው ሁሉ የሕዝቡን ድምፅ ለመቀልበስ ሕጋዊ ሽፋን አድርጎ በተገቢ ተጠቅሞበታል። ያ "ውል" የሕዝብን ድል አሣልፎ የሰጠና የኢሕአዴግ አምባ-ገነን አውራዎችን ከጉድ ያወጣ ብቻም ሣይሆን በኅብረቱ አመራር መኻል ግልጥ አለመጣጣምንና አለመተማመንን ያጫረ ጉዳይ ነበር ለማለት እደፍራለሁ።

በኅብረቱ በኩል ሁኔታዎች ለነፃና ርቱዓዊ ምርጫ እንዲመቻቹ የተቃዋሚው ጎራ አንድነቱን አጠናክሮ በጋራ አጀንዳ እንዲንቀሣቀስ ያላሰለሰ ጥረት እንዳደረገው ሁሉ፣ ድኅረ-ምርጫም ቢሆን ሕዝቡ በመራርና ክቡር መስዋዕትነቱ ያስመዘገባቸው ድሎቹ እንዳይነጠቁ ለለውጥ የቆመውና ከኢሕአዴግ ጋር በአደባባይ የሚፋለሙት ቅንጅትና ኅብረት በተመሣሣይ የግንዛቤ ሞገድ ላይ እንዲሆኑና በመኻላቸው ክፍተት ሣይኖር በጠራ ሕዝባዊ የጋራ አጀንዳ እንዲንቀሣቀሱ ፍላጎቱም ጥረቱም ነበር። በተለይም አገዛዙ ወደ-

ለየለት ሽብር መሸጋገሩና አንቅሮ በተፋው ሕዝብ ላይ የበቀል እርምጃ መውሰዱ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶችን አባላትና መሪዎችን ጭምር ማሰሩና ማንገላታቱ የማይቀር ጉዳይ በመሆኑ ሁለቱ መሪ ተቃዋሚ ድርጅቶች በየግል አጀንዳዎቻቸው ላይ አተኩረው በተናጠል ከመመታት ይልቅ የቅርብ ግንኙነት ፈጥረው በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ በጋራ መንቀሣቀስ የሚያስችሏቸውን መዋቅራዊ ትሥሥሮች እንዲፈጥሩና የአገዛዙን የቅልበሳ ዘመቻ እንዲያከሽፉ ኅብረቱ የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ ወስኖ ተንቀሣቅሷል።

በኅብረቱ በኩል ኅብረቱን ካሣሰቡትና በዝምታ ሊያልፋቸው ከማይችል ነገሮች ውስጥ አንዱ አቶ መለስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሩዋንዳው ዓይነት ጎሣን መሠረት ላደረገ የርስ-በርስ ፍጅት ለመዳረግ የነበራቸው አዝማሚያ ነው። በአገራችን "ኢንተርሃምዌ" ሊከሰት እንደሚችል በተደጋጋሚ ያሰሙትን ለፈፋ በዝምታ ማለፍ ያልፈለገውም አቶ መለስና አጋሮቻቸው ያን ለማድረግ ብቃቱም ፍላጎቱም እንደማይገዳቸው ያለፈ ታሪካቸው የማያጠራጥር በመሆኑ ነበር። ያንን አደጋ በሰበብነት ለማጫርና ለመቆስቆስም ከፋፋይና አምባ-ገነናዊ አገዛዛቸውን የሚቃወሙ የትግራይ ተወላጆች መኻል የተወሰኑትን አውጥቶ መረሸንም ሆነ የንግድ ድርጅቶቻቸው ላይ እርምጃ በመውሰድ በተቃዋሚው (በተለይም በሌሎች የጎሣ/የቋንቋ ክፍሎች) ላይ በመላከክ ትርምስ እስከ-መፍጠር ሊሄዱ እንደሚችሉ ግምት ነበር።

ስለሆነም ኅብረቱ በአንድ በኩል ይኽን ጎሠኝነትን መሠረት ላደረገ ሕዝብን ከፋፋይና ሰቆቃዊ አተራማሽ አደጋ ለመከላከል፣ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ በክቡር መስዋዕትነቱ ያስመዘገባቸውን ድሎች ላለማስቀልበስና ድምፁን ለማስከበር በሁለቱ ግንባር-ቀደም ተቃዋሚ ድርጅቶች (ቅንጅትና ኅብረት) የሚወሰዱ ውሳኔዎች ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖራቸው ማድረጉ አስፈላጊ ነበር። ለዚኽም ቀደም-ሲል እንደተገለጠው ከቅንጅቱና ከኅብረቱ ተመራጭ አባላት በተጨማሪ የአገር ሽማግሌዎችን፣ ምሁራንን፣ የልዩ ልዩ ሲቪክና የሙያ ማኅበራትንና ስብስቦች ተወካዮችን ያካተተ በመጀመሪያው ውሳኔ እስከ አንድ ሺህ አምስት መቶ በኃላ ግን የመሰብሰቢያ ቦታ ችግር አለ ሲባል ቁጥሩን በግማሽ በመቀነስ ሰባት-መቶ ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ የሁለት ቀን አገራዊ ጉባዔ በአዲስ አበባ እንዲደረግና በሦስተኛው ቀን በኢትዮጵያ ከተሞችና ኢትዮጵያውያን በርከት ብለው በሚገኙባቸው የዓለም ክፍሎች ጉባዔው ያሳልፋቸዋል ተብሎ የተጠበቁ ውሳኔዎችን በመደገፍ ሠልፍ እንዲደረግ አቅዶ ቅንጅቱ እንዲስማማበት ከተደረገ በኋላ ይኽንኑ እውን ለማድረግ ያላሰለሰ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

ምርጫው ከተገባደደ ጊዜ ጀምሮ ሁኔታዎች እየከፉ እንደሚሄዱ የተረዳው የኅብረቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አገዛዙ በተያያዘው ያመረረ የሽብር ዘመቻ ድርጅቶቹን ነጣጥሎ መምታት እንዳይችል ቅንጅትና ኅብረት በጋራ እንዲሠሩ የነበረው ጥረት እንዳይቋረጥ ተሞክሯል። በምርጫ መሣተፍም ይሁን አለመሣተፍ በሂደቱ የመሣተፍም ሆነ ያለመሣተፍን ያኽል መሠረታዊ መብት መሆን እንዳለበት ሁሉ፣ በታመነና በመረጃ በተደገፈ ሁኔታ የተጭበረበረ ውጤትን አለ-መቀበልና ያንን የተጭበረበረ "ውጤት" መሠረት አድርጎ በሚቋቋም አካል (ፓርላማ) አባል ሆኖ የመግባትና የአለ-መግባት ውሳኔ በቅድሚያ የተወዳዳሪውና ከዚያም ተወዳዳሪውን ያስሠለፈው ድርጅት ብቻ አንጡራ መብት ሊሆን እንደሚገባው እየታወቀ ከሕግ ተገዥነትና ከመብት ጋር ትውውቅ የሌላቸው የኢሕአዴግ መሪዎች የተቃዋሚውን (የቅንጅትና የኅብረትን) ተመራጮች "መጥኔ የሰጠኋችሁን ተቀብላችሁ" ወደ-ፓርላማ እንድትገቡ የሚል ቀጭን አስገዳጅ ትዕዛዝ በመስጠት ያንን ያልተቀበሉትን እያሣደደ በግፍ ማሠርን ሥራዬ-ብሎ ተያያዘው። ጠቅላላ የቅንጅት መሪዎችም የዚኽ አረመኔና ሕገ-ወጥ እርምጃ ሰለባ ሆነው ለእስር ከተዳረጉ በኋላ ቀደም-ሲል ከነበረው በባሰና ቅጥ-ባጣ መልኩ የተቃዋሚው አንድነት ተናጋ። አገዛዙም እጁን ሊያሣርፍባቸው የቻለውን ሁሉ በማደን የሚያስረውን አስሮ የተቀሩትን ደግሞ "የተገደዱ አጃቢዎች" ሆነው (የተወሰኑት በፍላጎት ሊሆን ይችላል) ፓርላማ እንዲገቡ በማድረግ እንዳሰላው ሁሉ ፓርላማው "ተቃዋሚውም የሚሣተፍበት" እንዲመስልና በሱ ደጋፊዎችና አባላት ብቻ የተሞላ ነው እንዳይባል ሲያደርግ፣ በዚያውም እግረ-መንገዱን በተቃዋሚው ጎራ ሊያሰፋው የሚችል ክፍተት እንዲፈጠርና ሕዝብም በተቃዋሚው ላይ ግራ እንዲጋባና ተስፋው እንዲቀጭጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ አደረገ።

ያም ሆኖ በኅብረቱ በኩል የግል አጀንዳውን በይደር ይዞ ቢያንስ አገዛዙ በሕገ-ወጥ መንገድና በግፍ ያሰራቸውንና ሕዝብ አመኔታውን ሰጥቶ የመረጣቸውን የቅንጅት መሪዎች የራሱም መሪዎች አድርጎ በመቁጠር እንዲፈቱ፣ እየታመሰና እየተሰቃየ ያለው ሕዝብ ላይ የሚደረገው እንግልት፣ አፈናና አፈሣ እንዲቆም፣ የሕዝቡ ድምፅ እንዲከበር፣ ወዘተ.. አንድ ላይ በመቆምና የጋራ *"የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል"* በማቋቋም የተባበረ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲቻል ከአገር-ውጭ የቅንጅት ውክልና ያላቸውን ወገኖች በአካል በማግኘትም ሆነ ደብዳቤ በመጻፍ ሣይታክት ወትውቷል፡፡ በዚኽ የመተባበር ጉዳይ ላይ ከተደረጉ ልውውጦች መኻል የሚከተሉት በምሣሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡
http://edhum.net/administrator/uploads/press_release/1e319_Kinjit%20NA%20Response%20letter%20to%20UEDF.pdf, http://edhum.net/administrator/uploads/press_release/6fc30_UEDF-letter%20to%20Kinijit%20NA,%20May%207,06.pdf,
http://www.edhum.net/administrator/uploads/press_release/b9c1b_UEDF-Letter%20to%20Kinijit-2,Dec.,05.pdf

በመረጃ እጥረት ምክንያት ሊሆን ይችላል አንዳንድ ወገኖች በኅብረቱ ስም ተወዳድረው ወደ-ፓርላማ የገቡትን አባላት እርምጃ በጥሬው ወስደው ኅብረቱን በ"ከሃዲነት" የከሰሱና የወቀሱ እንደ-ነበር ይታወቃል፡፡ ይሁንናም ወደ-ፓርላማ መግባትና አለመግባትን በተመለከተ የተወሰደውን ውሳኔ ኅብረቱ በአንድ ወቅት እንዲኽ ሲል ያስቀምጠዋል፡፡
*"ፓርላማ መግባት-አለመግባት በሚለው ጉዳይ ላይ ኅብረቱ አንዳች ቁርጠኛ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት፣ ምንም እንኳ የሕዝብ ድምፅ በጠራራ ፀሐይ በተሰረቀበትና ባለተከበረበት፣ ሕዝቡም ድሌን አሳስነጥቅም ብሎ በሚተናነቅበት ሁኔታ አገዛዙ ለወሰደው የሸፍጥና የማጭበርበር እርምጃ "ሕጋዊ" ሽፋን ከመሆን የማይዘልና ትግሉን በእጅጉ ወደ-ኋላ የሚጎትትና ለልበሣ የሚያመቻች አደገኛ እርምጃ በመሆኑ ውጤቱ ከወዲሁ የሚታወቅና የምር ሊወሰድ ቀርቶ ከልብ ሊስተናገድ የማይገባው ጉዳይ እንደሆነ የታመነ ቢሆንም፣ የመጨረሻው ውሳኔ ግን ከቅንጅት ጋር ተመካክሮ በጋራ ሊደረግ እንደሚገባ የኅብረቱ አመራር ግንዛቤና ውሳኔ በመሆኑ የቅንጅቱን ከፍተኛ የአመራር አባላት ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሙከራው ስላልተሣካም ኅብረቱ በጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔውን ማድረግ የቻለው ፓርላማ የተባለው አካል ሊከፈት ጥቂት ቀናት ሲቀሩ ነበር፡፡"*

ለአገራችንና ለሕዝቧ በጎ በማሰብ እየታገሉ ያሉ ወገኖች ከአሁን በፊት የተሠሩ ስህተቶችን ሲደግሙ፣ እራሣቸውን አድክመው ሕዝብንም ለድል ለማብቃት ወደማይችሉበት አቅጣጫ ሲጓዙና የጋራ ትግሉን ባላሰቡት መልክ ይበልጥ ሲያወሣስቡት እንዲሁም አንዳንድ ሂደቶችም በተሣሣተ መልክ ሲቀርቡ ስለ-ተገነዘብኩ፣ ከኢዴኃቅ ጀምሮ የተደረጉ የጋራ ጥረቶችን በአጭር-በአጭሩ በመዳሰስ የተሠሩ ስህተቶችን በማረም፣ ግድፈቶችን በማስተካከልና ጠንካራና ጠቃሚ ልምዶችን በማጎልበቱ ረገድ ለቀጣዩ ትግላችን አስተዋፅዖ ሊያደርግና ሊረዳ ይችል ይሆናል ከሚል ቀና አስተሣሰብ ተነስቼ ጥረቶቹና ሂደቶቻቸውን ለማሣየት ሞክሬአለሁ፡፡ እስካሁን ከታዩት ውስጥ ስለ-ኢዴኃኅ በመጠኑ ዘርዘር ተደርጎ ቀርቧል፡፡ አንዳንድ ሰነዶች ዋቢ እንዲሆኑና በተጨማሪ መረጃነትና ማብራሪያ በመሆን እንዲጠቅሙ በማሰብ በእዝል ለማስቀመጥ ሞክሬአለሁ፡፡ በቀጣይ ስለ ቅንጅት፣ "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (AFD)" እና ስለ 'መድረክ' በአጭር-በአጭሩ ለማሣየት ሞክሬአለሁ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ስለ-ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) የማቀርበውን ለመቋጨት ያኽል ኅብረቱ የተመሠረተበትን መንፈስ ተከትሎ ባደረገው እንቅስቃሴና በተከተለው ሂደት የገጠሙትን እክሎችና እንዳሰበው ግቡን ለመምታት ያላስቻሉትን ምክንያቶች መቃኘቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

*ኅብረቱ ተልእኮውን ሙሉ-በሙሉ ለመወጣት ያላስቻሉትና የገጠሙት ችግሮች በአጭሩ፡-*
ኅብረቱ ከሱ በፊት ቀደም ብሎ ተመሥርተው እንደ-ነበሩ የጋራ ትግል መድረኮች ሁሉ መሠረታዊ የሚባሉ ችግሮችና እክሎች ገጥመውታል፡፡ ምንም እንኳን ኅብረቱ በአመሠራረቱም ይሁን በአደረጃጀቱና በአወቃቀሩ ከዚያ በፊት ከነበሩ የጋራ ትግል ጥረቶች የተገኙ ልምዶችን በጥሞና መርምሮና ከውድቀቶች ትምርት ቀስሞ የተቋቋመ ሠፊ መሠረት ያለው ድርጅት ቢሆንም፣ ልክ እንደ-ሌሎቹ ምክንያቶቻቸውን በአብዛኛው ከአወቃቀርና ከአደረጃጀት የሚስቡና ተያያዥነት ያላቸው የአመራርና የአሠራር ችግሮች እንዲሁም አጠቃላይ ቀውስና አፈና የበዛበት የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ያሳደረው ጫና ተደራርበውና

ተደጋግፈው በተቋቋመበት መንፈስ መሥራት የሚችለውን ያኽል እንዳይሠራና ግቡንም ለመታት ሣይችል ሽባ ሆኖ እንዲቀር ሆኗል፡፡

*ሀ) አወቃቀርና አደረጃጀት፡-* ከአሁን በፊት እንደተጠቀሰው ኅብረቱ የተከተለው አደረጃጀትና ይኸንኑ አደረጃጀት ያንፀባረቀው አወቃቀሩ በሁለት መልክና ዘርፍ ያሉ አደረጃጀቶችን፣ ማለትም በአንድ በኩል በአገር-ውስጥና ከአገር-ውጭ፣ በሌላ በኩል ኅብረ-ብሔራዊ (አገር-አቀፍ) እና የአካባቢ/ብሔረሰብ/ጎሣ አደረጃጀት ይዘው የተዋቀሩትን በማጠፍ <u>በኢትዮጵያ አገራዊ ማዕቀፍ ሥር</u> በአንድ ሠፊ ድርጅታዊ መዋቅር ያስተሣሰረ ነበር፡፡ የሥርዓት ለውጥ ለማስገኘት የሚደረገውን ትግል አግላይነት በሌለው አንድ-ወጥ አሠላለፍ እውን ለማድረግ የተሻለ አማራጭ እንዲሆን፣ በማንኛውም ጊዜ በአገሪቱ የማዕከላዊነት ክፍተት ቢፈጠር ሁነኛ ጊዚያዊ አማራጭ ሆኖ እንዲገኝና ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአገሪቱ የዘረጋው ሕዝብን በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅ አዲስ ፖለቲካዊ ጎሠኝነትን መሠረት ያደረገ መርዘኛና ከፋፋይ ሥርዓት ቀስ-በቀስ እንዲከስም የሚያደርጉ መቀራረቦች እንዲፈጠሩና መተማመን እንዲያብብ የተሻለ ሁኔታን ያስገኛል ከሚል ስሌትና ያንንም እምነት አንግቦ ነበር ይዞት የተነሣውን አደረጃጀትና አወቃቀር የተከተለው፡፡

በዚኸም መንፈስ በሂደት የኅብረቱ አባል ድርጅቶች መኻል በቂ መቀራረብ ተፈጥሮና መተማመን ዳብሮ ብዙዎቹ የመዋኃድ ዕድል ያገኙና ቁጥሩ እየበዛ የመጣው የተቃዋሚ ክፍል ሰብሰብ ብሎ የተሻለ ጥንካሬ ያለው መሠረተ-ሠፊ ብሔራዊ የአንድነት ኃይል ሊወጣው ይችላል የሚል ተስፋ በብዙዎች ዘንድ ነበር፡፡ ሆኖም ግን እንደ-ኢሕአዴግ ዓይነት ኅልውናውን ሕዝብንና ተቃዋሚውን በመከፋፈል ላይ የመሠረተ መሠሪና አፋኝ ሥርዓትን በብቃት ለመዋጋት እያንዳንዱ ለጋራው መስዋዕት መሆንን፣ ክፍፍልን ያስወገደና አንድነቱን ያጠናከረ አደረጃጀትንና አንድ-ወጥ አወቃቀርን የሚጠይቀው የጋራ ትግል፣ ከጋራው ይልቅ ለተናጠሉ ጥቅም ያዘነበለው አስተሣሰብና አመለካከት ያጠቃው የድርጅቶች ታሪክ የጋራው ጥረት ላይ ሊኖር የሚገባውን ትኩረት አንቅዞታል፡፡

በተጠቀሰው መልክ የተደራጀው ኅብረት እያንዳንዱ አባል ድርጅት የየራሡን ቤት (ጣራውንም ግድግዳውንም) እንዳለ ይዞ የተዋቀረና እንደሚጠበቅበት ሣይሆን እንደ-ችሮታው ካለው እየመጠነ ቀንሶ ለጋራው የሰጠ በመሆኑ ድርጅቶች ከየግላቸው ይበልጥ ለጋራው በማድረግና በጋራውና ለጋራው ሥራ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ከመሥራትና የጋራው ከተናጠሉ ሊያገኝ ከሚገባውና ከሚጠይቀው ጥረት ይበልጥ ከጋራው ቆንጥሮና ተናጠሉ ከወሉ (ከኅብረቱ) በሚያገኘው ጥቅም  ላይ ያተኮረ አካሄድን መከተሉ አይቀሬ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የፖለቲካ ምኅዳሩ ባልጠበበበትና ዴሞክራሲ መሠረት በያዘበት ኅብረተሰብና የመድብለ-ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት በተደላደለበት ሁኔታ ለሚደረግ አዘቦታዊና መደበኛ የፖለቲካ ትግል ይኸ ዓይነት አወቃቀር ሊሠራ መቻሉ ቢታወቅም፣ የኅብረቱ አወቃቀር ከእያንዳንዱ አባል ድርጅት የፖለቲካ እምነትና የአደረጃጀት ዘይቤ አኳያ ሲመረመር በሥልጣን ላይ ያለውን ክፍል ለመታገልና የሽግግር ሂደትም በመከተሉ አስፈላጊነት ላይ ስምምነት የነበር ከመሆኑ ውጭ ከኢሕአዴግ “ሕገ-መንግሥት” ጀምሮ ድኅረ-ኢሕአዴግ እንዲመጣ በሚፈለገው የሥርዓት ለውጥ ላይ በሁሉም ዘንድ ከደፈናዊ “መግባባት” የወጣ ተመሣሣይ፣ ሙሉና ግልጥ አቋም ነበር ማለት አይቻልም፡፡ አንዳንዱ “ሾላ በድፍን” ዓይነት ስምምነት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለዚኸ ምክንያቱ፣ ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው ምንም እንኳን የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ኅብረቱን ሲመሠርቱም ሆነ በኅብረቱ ተካትተው ለመታገል ሲወስኑ የቆሙባቸውንና የሚታገሉላቸውን ዓላማዎች በኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ማዕቀፍ ውስጥ ለማስተናገድ በመስማማት ቢሆንም፣ አንዳንዶቹ አባል ድርጅቶች የተከተሉት የአደረጃጀት ዘይቤ ከሌሎቹ አባላት የፖለቲካ እምነትም ሆነ በኅብረት ደረጃ ያለውን ከፋፋይ ሥርዓት እንደ-ሥርዓት ለማስወገድ ከተወሰደው አንደምታዊ ስምምነት ጋር ሊጣጣም እንደማይችል የታወቀ ነው፡፡ የአንዳንዶቹ የአደረጃጀት ዘይቤ ኅብረቱ በይፋ ከቆመበት ፖለቲካዊ ብሔረሰብን/ጎሣን መሠረት ያደረገ ከፋፋይ ሥርዓትን የማይቀበል መሠረታዊ አቋም ጋር የማይጣጣምና ድርጅታዊ የፖለቲካ እምነታቸው ከኢሕአዴግ ሠፈር የሚደመሩና ከኢሕአዴግ ጋር ያላቸው ልዩነት የፖለቲካ ፍልሥፍና ሣይሆን ምናልባትም የአካሄድና የአፈጻጸም ከመሆን የማያልፍ እንደ-ሆነ ግልጥ ነው፡፡

***በክፍል ሃያ-አራት ይቀጥላል……***